12-06-2022

# ውታፍ ነቃይ

ከጣሰው እንደልቡ

የኦሮሚያ ፕሬዜዳን ሽመልስ አብዲሳ "ኢትዮጵያን ወደ ወደ ገዳ ስርዓት እንመልሳታለን.. " ካለ በኋላ ለብዙ ኢትዮጵያውያን መነጋገሪያ ርእስ ሆኖዋል፡፡ ብዙዎችም ለመሆኑ የገዳ ስርዓት ምን አይነት ነው? ብለው እንዲመረምሩ መንገድ ከፍቷል፡፡ "ለሰይጣንም ዋጋውን አትንፈጉት" እንደሚባለው ሽመልስ አብዲሳ የኦሮሞ ብሄረተኞችን አላማ ስለነገረን አለማመስገን አይቻልም፡፡

ለዛሬ መነሻ መጽሀፌ አድርጌ የመረጥሁት መጽሀፍ በአባ ባህሪ የተጻፈውን "ዜናሁ ለጋላ" የሚለውን መጽሀፍ ነው፡፡ ወደ ጽሁፌ ከመግባቴ በፊት ግን ሁለት ነገር ማለት እፈልጋለሁ፡፡

1ኛ - መጽሀፉ የተጻፈው በጊዜው በነበሩ የአይን ምስክር በአባ ባህሪ ሲሆን፣ ይህ መጽሀፍም ዛሬ ኦሮሞ ስለሚባለው ነገድ ዋነኛ የታሪክ ምንጭ ነው ቢባል ከእውነት አይርቅም፡፡ በኦሮሞ ታሪክ ምርምርም ያደረገ ይሁን፣ የዛሬዎቹ የኦሮሞ ብሄረተኞች ለታሪክ ጥናታቸውም ሆነ ለዶክትሬታቸው እየተናነቃቸውም ቢሆን የሚያጠኑትና የሚጠቅሱት ይሄንኑ መጽሀፍ ነው፡፡

2ኛ - ይሄንን መጽሀፍ የኢትዮጵያ ህዝብ በአማረኛ እንዲያነበው ከግእዙ ለተረጎሙልን ለፕሮፌሰር ጌታቸው ኃይሌና፣ በኢንተርኔትም ገብተን እንድናነበው እድሉን ለሰጠን ለኢትዮፓትሪዎት ድህረ ገጽ ምስጋናዬን ላቀርብ እወዳለሁ፡፡

በመጨረሻም እኔ እንደግለሰብ የነገድ ስም በመቀየር የኢትዮጵያን የአለፈ ታሪክ ለመቀዬር መብትም ሆነ ስልጣን አለኝ ብዬ ስለማላምን፣ በመጽሀፉ ላይ እንደሰፈረውና እስከ ቅርብ ጊዜ ድረስ ነገዱ ይጠራበት እንደነበረው ጋላን - ጋላ እንጂ ኦሮሞ ብዬ መጥራት የለብኝም የሚል እምነት አለኝ፡፡ ስለዚህ በ16ኛው ክፍለ ዘመን የነበረውን የጋላ ወረራ - የጋላ ወረራ እንጂ የኦሮሞ ወረራ ብዬ ህዝብንም ሆነ እራሴን መዋሸት አልፈቅድም፡፡

ይሄንን ካልሁ በኋላ፣ አባ ባህሪ "ዜናሁ ለጋላ" በሚሉት መጽሀፋቸው፣ የጋላ ነገድ የኢትዮጵያን መሬት ከረገጠበት ጊዜ ጀምሮ የአምስቱን ሉባዎች፣ ማለትም ከሜልባክ ሉባ እስከ ሚቼሌ ያለውን ጽፈውልናል፡፡ ዛሬ አቶ ሽመልስ የሚለን ኢትዮጵያን በገዳ ስርዓት የምትተዳደር ሀገር ለማድረግ ከሆነ፣ በማንም አእምሮ ቀድሞ የሚመጣው ጥያቄ፣ ገዳ ምን አይነት የመንግስት አስተዳደር ቅርጽ አለው ? የሚል ጥያቄ ይሆናል፡፡

ክቡር አቶ ይልማ ደሬሳ "የ16ኛው ክፍለ ዘመን ታሪክ" በሚሉት መጽሀፋቸው - ገዳን የመንግስት አስተዳደር ስርዓት ቅርጽ ያለው ነው ከማለት ይልቅ ስርዓት መባል ደረጃ ያልደረሰ "ድርጅት" ነው ሲሉ ይገልጹታል፡፡

ፕሮፌሰር ሃይሉ ላሬቦ በርዮት ራዲዮ ከቲዎድሮስ ጋር ባደረጉት ውይይት ደግሞ "የድንጋይ ዘመን ስርዓት ነው፡፡" ብለውታል፡፡ ከነዚህ ከሁለቱ ሰዎች ትርጉም ተነስተን በጊዜው የአይን ምስክር የነበሩት እና በጋላ ወረራን ታሪክ ተቀዳሚና እና አቻ የሊለው የታሪክ ምንጭ ሆኖ የሚጠቀሰውን "ዜናሁ ለጋላን" ስናነብ፣ የገዳ ስርዓት በመውረርና በመግደል ላይ ብቻ የሚያጠነጥን፣ ብዙ ሰው የገደለን የሚያወድስና የሚያከብር፣ ሀገር ለማስተዳደር ቀርቶ ክቡር አቶ ይልማ ደሬሳ እንዳሉት

የድርጅትነት ደረጃ ያልደረሰ ሆኖ እናገኘዋለን፡፡ ለዚህ መረዳቴ፣ አንባቢም ሆነ አድማጭ "ዜናሁ ለጋላን" አንብቦ የራሱን ፍርድ እንዲሰጥ እጠይቃለሁ፡፡

ገዳ - የግድያ ባህል የሚሸልም የሚያወድስ የወረራ ስርዓት ወይም ክቡር አቶ ይልማ እንዳሉት ድርጅት ነው፡፡ በስርአትነት እንየው ካልን -የአስተዳደር ስርዓት ሳይሆን የወረራ ስርዓት ነው፡፡ ለዚህም ብዙ የገደለ ወደ ሉባ መደብ ይገባል፣ የሚገለው ደግሞ ትልቅ አውሬ ወይም ሰው ነው፡፡ የሚገደለው ሰው ጋላ እስካልሆነ ድረስ ህጻን- ሽማግሌ፣ ወይም ሴት -ወንድ ብሎ አይመርጥም፡፡ ነገር ግን ጋላ - ጋላን ከገደለ ለምጽ ይይዘዋል የሚል እምነት ስላለ ጋላ - ጋላን አይገልም፡፡ ታዲያ በዚህ የገዳ ስርዓት አንድ ሉባ የሚያስተዳድረው 8 ዓመት ነው፡፡ በየ8 አመቱ ተራ ገብተው አንዱ ሉባ ለሚቀጥለው ሉባ ከመልቀቁ በፊት ዘመቻ ያደርግና ቀዳሚው ሉባ ያልወጋውን ሀገር ሄዶ መውጋት፣ መዝረፍና መግደል ነው፡፡ መስፈርቱ መግደል በመሆኑ አንድ ሉባ ስልጣኑን የሚያገኘው በጨካኝ ሁኔታ በመግደሉ እና በመዝረፉ ነው፡፡ ሰው ወይም ትልቅ አውሬ መግደል ወደ ሉባ መደብ ለመግባት ብቻ ሳይሆን እንድ ጋላ ሚስት ለማግባትም መግደል አለበት፡፡

ቁሮ የሚባለው ከወጣትነት እድሜ ክልል አልፎ ለጋብቻ ዝግጁ መሆኑን የሚያስመሰክረው ሰው ወይም ትልቅ አውሬ በመግደል ነው፡፡ ካልገደለ ጸጉሩን አይቆረጥም፣ አባ ባህሪ እንደሚነግሩን - የጸጉራቸው ማደግ ቅማል እየፈጠረ ለመግደል ያተጋቸዋል ይላሉ፡፡ የገደለ መሀል አናቱ ላይ ጸጉር አስቀርቶ ሌላውን ይላጨዋል፡፡ ነገሩን ለማሳጠር ገዳ - ብዙ የገደሉን ከፍ - ክፍ የሚደርግና የሚያስፎክ፣ ጋላ ያልሆነውን ህዝብ "ዲና" ወይመ "ጠላት" ብሎ የሚፈርጅ፣ ፕሮፌሰር እስቃኤል እንደነገሩን "ሰው ከውሀ ወጣ" ብሎ የሚያምን፣ ከክርስትናም ሆነ ከእስልምና ወይም ከሌላው እምነት ሁሉ የተለዬ እምነት ያለው ነው፡፡

የአባ ባህሪ መጽሀፍ የሚያሳዬን የ5 ሉባዎችን ወይም 40 ዓመት ታሪክ የሚተርክ ሲሆን እሱም ጋሎች የኢትዮጵያን ድንበር አልፈው ከገቡበት ከመጀመሪያው ሉባ ከሜልባክ ዘመን ይጀምራል፣ ከላይ እንደጠቀስሁት አንድ ሉባ የሚቆየው 8 ዓመት ስለሆነ ሜልባክን የተካው ቡዳብ ይባላል፤ ከቡዳብም በኋላ ቲሎሌ ተካው፣ እሱንም ከስምንት ዓመት ቢፎሌ ተካው፡፡ ቢፎሌን ግን ከሌሎች ሉባዎች የሚለየው፣ ከሱ የቀደሙት ከጋላ ውጭ የሆነውን ህዝብ "ዲና" ወይም "ጠላት" ብለው ያጠፉት ነበር፡፡ ቢፎሌ ሉባ ሲሆን ግን "ገርባ" ወይም ባሪያ ብሎ ከሞት የተረፈውን ህዝብ በሞጋሳ ስርዓት ሁለት ምርጫ ሰጠው፡፡ ይሄውም ፣ኛ- እኛን መስላችሁ - የእኛን ቋንቋ እየተናገራችሁ፣ የእኛን አባት የእናንተ አባት አድርጋችሁ መኖር ትችላላችሁ፣ ወይም 2ኛው ምርጫ ሞት ነው የሚል ነበር፡፡ በዚህም ምክንያት ህዝቡ ከሞት ለመሸሽ የሞጋሳ ልጅ ሆነ፡፡ ሞጋሳ ማለት ጋላ ያልሆነ፣ ቋንቋውን፣ ባህሉን፣ ማንነቱን፣ አባቱን፣ ታሪኩን ትቶ፣ ከሞት ለማምለጥ ሲል የጋላ ማንነት የተቀበለ ማለት ነው፡፡ ከቢፎሌ በኋላ የመጣው ሉባ ሚቺሌ ይባላል፡፡ አባ ባህሪ እስከ አምስተኛው ሉባ የተረኩልንን ሰፋ አድርጎ ለመረዳት መጽሀፉን ማንበብ ያስፈልጋል፡፡

በዚህ በገዳ ስርዓት ፣ እንደፕሮፌሰር ኃይሌ ላሬቦ ከሆነ ቢያንስ አንድ ሚሊዮን ህዝብ አልቋል፡፡ እንግዲህ የእነ ሽመልስ እና ባጠቃላይ የኦሮሞ ብሄረተኞች ትግል ይህን የወረራ ስርዓት ለመድገም ከሆነ፣ ዛሬ ጊዜው ፲6ኛው ክፍለ ዘመን አለመሆኑን እንዲረዱ ያስፈልጋል፡፡ ኢትዮጵያ ቀደምት የመንግስት ስርዓት ከነበራቸው ጥቂት ሀገሮች አንዷ መሆኑዋን ታሪክ ይመሰክራል፡፡ በአሁኑ ዘመን ይህ አይነት ስርዓት ይገባናል ብሎ የሚቀበል ኢትዮጵያዊም ይኖርል ብዬ አላምንም፡፡ ሚሊዮን ተረት ተረት ቢፈበረክም አንድን እውነት ለጊዜው ያደበዝዛት እንደሆን እንጂ አያጠፉትም፡፡ ስለዚህ የኦሮሞ ብሄረተኞች አደብ ግዙ ሊባሉ ይገባል፡፡